# አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት

ማኅበረ ሰላም ሰ/ት/ቤት
ደብሊን

# አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት

1. ቅዱስ እንድርያስ
2. ቅዱስ በርቶሎሚዎሰ
3. ቅዱስ ያዕቆብ (ታላቁ)
4. ቅዱስ ያዕቆብ (ታናሹ)
5. ቅዱስ ፊልጶስ
6. ቅዱስ ዮሐንስ (ወንጌላዊ)
7. ቅዱስ ማቴዎስ
8. ቅዱስ ጴጥሮስ
9. ቅዱስ ስምዖን
10. ቅዱስ ይሁዳ
11. ቅዱስ ቶማስ
12. ቅዱስ ማትያስ



# ቅድስት ሃገር በጌታ ልደት ዘመን



# 1-ቅዱስ እንድርያስ

- ትውልዱ አይሁዳዊ (ቤተሳይዳ) ይሁን እንጂ ስሙ የግሪክ ነው ትርጉሙም ኀበዝ፤ቆራጥ ማለት ነው::
- ከጴጥሮስ ጋር ወንድማማች ናቸው::
- ሥራቸው ከአባታቸው ጋር ዓሣ ማጥመድ ነበር::
- በመጀመሪያ የዮሐንስ መጥምቁ ደቀ መዝሙር ነበር::
- ከሁሉ አስቀድሞ ወደ ሐዋርያነት የተጠራ እርሱ ነው::
- ጌታ 5000 ሰው በመገበ ጊዜ «በኛ ዘንድ 2 ዓሣ እና 5 እንጀራ የያዘ አለ» ብሎ የተናገረ እርሱ ነው::
- በሰማዕትነት ያረፈው ፓትራስ (በግሪክ) በምትባል ከተማ በ «X» ምልክት መስቀል ተሰቅሎ ነው:: ሳይሞትም ለሁለት ቀን ያህል እየመሰከረ ቆይቱዋል::

# ሰማዕትነት ሲቀበል






ቤተክርስቲያኑ በግሪክ ፓትራስ ከተማ

# 2-ቅዱስ በርቶሎሚዎስ

- የስሙ ትርጉም የቶሎሚዎስ ልጅ ማለት ነው
- አውነተኛ ስሙ ናትናኤል ነው ትርጉሙም የአምላክ ስጦታ ማለት ነው::
- የቃና ዘገሊላ ሰው ነው::
- ጌታችን «ተንኮል የሌለበት በእውነት የእስራኤል ሰው እነሆ» ብሎ የመሰከረለት ነው::ዮሐ. 1:49
- በሕንድ በሜሶፖታሚያ ፐርሺያና በግብጽ ከሰበከ በሁዋላ ወደ አርማንያ መጥቶ በአልባኖፖሊሰ ከተማ ከነሕይወቱ ቆዳው ተገፎ ከዚያም አንገቱ በሰይፍ ተቆርጦ ሰማዕትነትን ተቀበለ:: ይህን የመሰለ አሰቃቂ ፍርድ የፈረደበትም ንጉስ ወንድሙን ስላሳመነበት ነው::

# ሐዋርያው ቅዱስ ናትናኤል በሕይወቱ እያለ ቆዳው ሲገፈፍ



# 3-ቅዱስ ያዕቆብ (ታላቁ) (1)

- የዮሐንስ ወንጌላዊ ወንድም ነው::
- «ታላቁ» የተባለው ከ«ታናሹ ያዕቆብ» በእድሜ ስለሚበልጥ ነው::
- ከወንድሙ ከዮሐንስ ወንጌላዊ ጋር ዓሣ ሲያጠምዱ ለሐዋርያነት ተጠራ::
- ጌታ «ቦኤኔርጌስ» የሚል መጠሪያ ለርሱና ለዮሐንስ ሰጥቶዋቸዋል፤ «የነጎድጉዋድ ልጆች» ማለት ነው::
- ከጴጥሮስና ከዮሐንስ ጋር የታላላቅ ምስጢራት ተካፋይ ነበር ለምሳሌ ጌታ የጴጥሮስን አማት ሲፈውስ፣ ወለተ ኢያኢሮስን ከሞት ሲያስነሳ፣ በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን ሲገልጥና በጌቴሴማኒ ሐሙስ ማታ በአትክልቱ ቦታ::

# ቅዱስ ያዕቆብ (ታላቁ) (2)

- የያዕቆብና የዮሐንስ እናታቸው ሰሎሜ አባታቸው ደግሞ ዘብዴዎስ መሆናቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሰዋል::
- «አንዱን ልጄን በቀኝህ ሌላውን በግራህ...»(ማቴ.20:20-28)
- ከሐዋርያት ሰማዕት ለመሆን የመጀመሪያ ነው ይህም በ44 ዓ.ም. አይሁድን ያስደሰተ መስሎት ንጉስ ሄሮድስ አግሪጳ ነው ያስገደለው:: (የሐዋ. ሥራ 12:1-2)
- አሳልፎ የሰጠውም ሰው በድረጊቱ ተጸጽቶ እየተከታተለ ይቅርታ እየለመነ ቢያስቸግረው ቆም አለና «ሰላም ላንተ ይሁን» አለና አቅፎ ሳመው:: ይህም ሰው የዚያኑ ጊዜ አምኖ አብሮት አንገቱን ተሰይፎ ሰማዕት ሆኑዋል::

# ሰማዕትነት

- አንገቱን በሰይፍ ሲቆረጥ



# 4-ቅዱስ ያዕቆብ (ታናሹ) (1)

- የእልፍዮስ ልጅ፣ የጌታ ወንድም፣የማርያም ልጅ የዮሳ ወንድም በመባል ተጠርቱዋል፡፡
- እናቱ የእመቤታችን እህት እንደሆነች ይታመናል፡፡
- ቅዱስ ይሁዳ (የአስቆሮቱ ያይደለ) ወንድም ነው፡፡
- ሁለቱም ለሐዋርያነት የተጠሩት ጌታ ማስተማር በጀመረ በሁለተኛው ዓመት ነው፡፡
- በመጀመሪያው የኢየሩሳሌም የሐዋርያት ጉበኤ ሊቀመንበር ነበር፡፡
- የመጀመሪያው የኢየሩሳሌም አጲስ ቆጶስም ነበር፡፡
- ተወዳጅና ቅን ሰው ከመሆኑ የተነሳ በአይሁድ ዘንድ እንኳዋ ሳይቀር «ጻድቁ» በሚል ቅጽል ስም ይጠራ ነበር፡፡

# ቅዱስ ያዕቆብ (ታናሹ) (2)

- ከትንሳኤው በሁዋላ ጌታችን በታለቅ ግርማ ተገልጦ ታይቶታል:: 1ቆሮ. 15:7
- አንድ መልእክት ጽፎአል:: ይህም የያዕቆብ መልእክት በመባል የሚታወቀው ነው::
- በሕይወት ዘመኑ ሁሉ «ድንግላዊ ሆኖ ኖረ፣ወይንም ሆነ ሌላ ጠንካራ መጠጥ ጠጥቶ አያውቅም፣ሥጋም ከቶ አልበላም፣ምላጭም ጠጉሩን ነክቶት አያውቅም፣ቅባት ተቀብቶ ሰውነቱንም ታጥቦ አያውቅም፣ጫማም አድርጎ አያውቅም፣አንዲት ብቻ ልብስ ነበረችው፣ለጸሎት ከቁመት ብዛት እግሩ ያበጠ (ዝሆኔ) ነበር፣ በስግደት ብዛትም ጉልበቱና ግንባሩ እንደግመል ሸሆና ደድሮ ነበር»

# ሰማዕትነት በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ (1)

- ብዙዎች በጌታ በማመናቸው ምክንያት አይሁድ ለፋሲካ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የሚሰበሰበውን ሕዝብ ክርስቶስ የተባለው ኢየሱስን እንዲክዱ አንዲያግባባላቸው ለመኑት፤ ህዝቡ ሁሉ እርሱን ይሰሙት ነበርና:: በዚህም ሰበብ ወደ ቤተ መቀደሱ ጫፍ አወጡና ለህዘቡ በግልጥ አንዲናገር ለመኑት:: እርሱም በታላቅ ድምጽ «ስለ ሰው ልጅ ስለምን ትጠይቁኛላችሁ? እርሱ በሰማያት በልዑሉ ቀኝ ተቀምጦአል፤ በሰማይ ደመና ተጭኖም ይመጣል» ሲል ተናገረ:: ብዙዎችም ሰምተው እግዚአብሔርን አከበሩ «ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ» እያሉ ተናገሩ:: አይሁድም በዚህ ጊዜ እጅግ ተቆጥተው «ጻድቁም እንኳዋን ተሳሳተ» ብለው ወደ መሬት ገፍትረው ጣሉት:: ነገር ግን አልሞተም ነበር ከመሬት ያሉትም ድንጋይ እያነሱ ይወግሩት ነበር እረሱ ግን እንደምንም ተንበርክኮ «አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» አለ:: ከነርሱም አንዱ በትር አንስቶ ራሱን መታው በአንድ ጊዜም ሰማዕትነትን ተቀበለ:: በዚያው በቤተ መቅደሱ አጠገብ ቀበሩት::

# ሰማዕትነት በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ (2)



# 5-ቅዱስ ፊልጶስ

- በመጀመሪያ የዮሐንስ መጥምቁ ደቀመዝሙር ነበር፡፡
- ናትናኤልን የጠራው እርሱ ነው፡፡
- ትውልዱ በቤተሳይዳ በገሊላ መንደር ነው፡፡
- ጌታችንም የመጀመሪያውን ተአምር ጨምሮ ብዙ ምልክቶችን በቤተሳይዳ አድርጉዋል፡፡5000 ሰዎችን የመገበበት ቦታ ከፊልጶስ መኖሪያ ከተማ ብዙም አይርቅም፡፡
- «አብን አሳየንና ይበቃናል» ሲል የጠየቀ እርሱ ነው፡፡ (ዮሐ. 14፥8)

# ሰማዕትነት

- በግሪክ የተለያዩ ከተሞች ከሰበከ በሁዋላ ሂራፖሊሰ በተባለች ከተማ ዶሚቲያን በተባለ ንጉስ ተዕዛዝ በእባብ የሚያመልኩ አሕዛብ እርሱንና ናትናኤልን ቁለቁል ሰቀሉዋቸው ነገር ግን በፊልጶስ ጸሎት ከፍተኛ የመሬት መንቀጥቀጥ ተከሰተ ሰዎቹም ፈርተው ባወረዱዋቸው ጊዜ ናትናኤል ሲተርፍ ፊልጶስ ግን አርፎ ነበር:: አብራው የመትዞር ማሪያና የተባለችው እህቱ በዚያው አስቀብራው ከናተናኤል ጋር ወደ አርማንያ ሄዳለች::

# 6-ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ

- የያዕቆብ (ታላቁ) ወንድም ነው።
- ከሐዋርያት ሁሉ በእድሜ ትንሽ ነበረ ስለዚህም ከሁሉ መጨረሻ ነው ያረፈው (የተሰወረው)።
- በተለይ የሚታወቅበት ደግሞ «ጌታ ይወደው የነበረ ደቀ መዝሙር» ተብሎ ነው።
- በአይሁድ ሊቀካህናት ዘንድ በደንብ የታወቀ ነበር።
- ወንጌሉን፣ ሁለት መልእክታትና ራዕይን ጽፉዋል።
- ዮሐንስ፣ ያዕቆብና ጴጥርስ ከጌታ እርገት በሁዋላ በኢየሩሳሌም የነበሩ ዋኖች ነበሩ።
- እመቤታችን በአደራ የተሰጠችው ለእርሱ ነው

# እረፍት (1)

- ዶሚቲያን ዮሐንስንም ለማስገደል ከኤፌሶን ወደ ሮም አስሮ አስመጥቶት ነበር:: ነገር ግን በተከሰተው የመሬት መንቀጥቀጥ ተደናግጦ ፍጥሞ ወደምትባል ደሴት አጋዘው:: ራዕዩን የጻፈውም በዚህ ቦታ ሆኖ ነው::
- በ 96 ዓ.ም. ዶሚቲያን ሲያርፍ ወደ ኤፌሶን ተመለሰ ወንጌሉንም በዚህ ጊዜ እንደጻፈው ይታመናል::
- በኢፌሶን ሲኖር በእርግና ብዛት መንቀሳቀስ ባለመቻሉ በአልጋ ተሸክመው ወደ ጉባኤ አምጥተው ያስቀምጡት ነበር::
- የዘወትር ትምህርቱም «ልጆቼ፤እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚል ነበር:: ከእለታት አንድ ቀን «ለምን ይህንኑ ቃል ሁል ጊዜ ትደጋግማለህ?» ብለው ቢጠይቁት«ምክንያቱም ይህ የራሱ የጌታ ቃል ነው፣ እናንተም እርሱን ከጠበቃችሁ ይበቃችሁዋል» አላቸው::

# እረፍት (2)

- ዮሐንስ እረፍቱ በዚሁ በኤፌሶን ነው:: የኢኦተቤክ ዮሐንስ እንደተሰወረ ታስተምራለች:: በዚህ ጊዜም የ94 ዓመት አረጋዊ ነበር:: ታሪኩም «ዮሐንስ የመሄጃው ሰዓት እንደደረሰ አውቆ ደቀ መዝሙሩን ቦታው ጋር ወስዶ ለመቀበሪያዬ የሚሆን ጉድጉዋድ ቆፍር ይለዋል:: ደቀመዝሙሩም ይህንኑ አደረገ:: እንደጨረሰም ሂድና ሌሎች ወንድሞችህን ጥራ ብሎ ላከው:: በተመለሰ ጊዜ ግን ቦታው ለምለም ሳር በቅሎበት መጎናጸፊያውና በትሩ በዚያ ወድቆ ተገኝቱዋል በዚህም ጌታ እንደተናገረው ሞትን ሳይቀምስ ተሰውሩዋል:: ማቴ. 16:28 ፤ ዮሐ. 21:22

# 7-ቅዱስ ማቴዎስ

- የቀድሞ ስሙ ሌዊ ነበር በማርቆስ ወንጌል ደግሞ «የእልፍዮስ ልጅ» ተብሎ ተጠርቷዋል::«እልፍዮስ» የታናሹ ያዕቆብ አባት አይደለም::
- ጌታ ደግሞ «ማቴዎስ» ብሎ ጠርቶታል፤ «የያህዌ ስጦታ» ማለት ነው::
- ትውልዱ ገሊላዊ ነው ሥራውም ለሮማውያን ግብር (ቀረጥ) ከአይሁድ መሰብሰብ ነበር::
- ቀራጭ ማለትም አይሁድ ገበታ የማይካፈሉት፣በጋብቻ የማይዛመዱት፣በአምልኮ የማይተባበሩት፤ በማናቸውም ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋዋሞች የማያስገቡት ነው:: ባጭሩ ከሁሉ የከፋ «ኃጢአተኛ» ማለት ነበር::

# መጠራቱ

- ጌታም «ተከተለኝ» ሲለው በግብር መሰብሰቢያ ገበታው ላይ ተቀምጦ ሥራውን እየሰራ ነበር::
- የተጠራውም ጌታ ማስተማር በጀመረ በሁለተኛው ዓመት ነበር::
- ቀረጥ መሰብሰቢያውም ቅፍርናሆም ስለነበር ጌታ ስላደረገው ተአምራት ብዙ ሳይሰማ አልቀረም:: በቅጽበት ጥሪ ግን ሁሉን ጥሎ መከተሉ ሁሉን አስገርሙዋል በአፍአ «ተከተለኝ» ሲለው በውስጥ በማይነገር ምስጢሩ ልቡንም ስቦታል ሲሉም ያደንቃሉ::
- ወንጌሉንም ከአይሁድ ለተጠመቁ ክርስቲያኖች በሚናገሩበት በአረማይክ (ሂብሩ) ጽፎላቸዋል

# ሰማዕትነት

- በይሁዳ ብዙ ክርስቲያኖችን አፍርቶ ሌሎችን ደግሞ ለማስተማር ወደ «ምስራቅ» እንደሄደ ይተረካል:: ይህ «ምስራቅ» ግን የት እንደሆነ በውል አልታወቀም::ወደ ኢትዮጵያም መጥቶ ነበር በሰማዕትነት የሞተውም እዚህ ነው የሚሉ አሉ:: ነገር ግን ይህ የተረጋገጠ አይደለም::
- በሰማዕትነት መሞቱን ብዙዎች ቢስማሙበትም መቼ፣የትና እንዴት እንደሞተ ግን ያወቀ የለም::

# 8-ቅዱስ ጴጥሮስ

- ትውልዱ፡ አባቱ (ዮና) ነገዱ ሮቤል የእናቱ ደግሞ ስምዖን ነው::
- ሰሙም በእናቱ ነገድ «ስምዖን» ተባለ ጌታ ግን «ኬፋ» አለው ትርጉሙም ዓለት ማለት ሲሆን በግሪክ ደግሞ «ጴጥሮስ» ይባላል::
- ከወንድሙ ከእንድርያስ ጋር ዓሣ አጥማጅ ነበሩ::
- ኩሉም በእድሜ የገፋ ነበር::
- ሁለት መልእክታትን ጽፎአል::

# ቅዱስ ጴጥሮስ (ሰማዕትነት)

- በኔሮ ቄሳር ዘመን በ64 ዓ.ም. በራሱ ጥያቄ ቁልቁሊት ተሰቅሎ ሰማዕትነትን ተቀበለ፡፡ ቦታውም በሮም ከተማ በኔሮ መናፈሻ ነው፡፡ በቦታው ዛሬ ታላቅ ቤተክርስቲያን ተሰርቶበታል፡፡



# የቅዱስ ጴጥሮስ ታሪክ በሐዲስ ኪዳን በሰፊው ተተርኮ አለ::(1)

- በባሕር ላይ መሄዱ፣
- በቂሳርያ የሰጠው ምስክርነት፣
- በደብረ ታቦር የጌታን ግርማ መለኮት ማየቱ፣
- ከዓሣ ሆድ አራት ድሪም አውጥቶ ግብር ስለመክፈሉ፣
- ትዳሩን ሁሉ በመተዉ ስለሚያገኘው መጠየቁ፣
- ጌታ እግሩን ሊያጥበው ሲል ስለመከልከሉ፣
- ሦስት ጊዜ ስለመካዱና ንስሐ ስለመግባቱ፣
- ትንሣኤን ስለማይቱ፣
- በጥብርያዶስ ጌታን ስለማየቱ፣
- «ግልገሎቼን»፣«ጠቦቶቼን»«በጎቼን» ጠብቅ ስለመባሉ፣
- ስለ ሞቱ መስማቱ

# የቅዱስ ጴጥሮስ ታሪክ በሐዲስ ኪዳን በሰፊው ተተርኮ አለ::(2)

- በይሁዳ ምትክ ሌላ እንዲመረጥ ስለመናገሩ፣
- በአንድ ቀን 3000 ሰው ስለማሳመኑ፣
- በመቅደስ አንካሳውን ስለመፈወሱ፣
- በሐናንያና በሰጲራ ስለመፍረዱ፣
- ጣቢታ የምትባልን ደግ ሴት እንዳስነሳ፣
- ቆርነሌዎስን እንዳጠመቀ፣
- በመልአኩ አማካይነት ከእስር ቤት ስለ መውጣቱ፣
- በመጀመሪያው የሐዋርያት ጉበኤ መናገሩ፤
- ወዘተረፈ.

# 9-ቅዱስ ስምዖን

- በተለይ የሚታወቀው «ቀናተኛው» በመባል ነው ይህም ለአይሁድ ሕግ መቅናቱን ይገልጣል። በተጨማሪም ከስምዖን ጴጥሮስ የሚለይበት ነው።
- ስለዚህ ሐዋርያ ብዙ የተመዘገበ ታሪክ የለም። ነገር ግን ግብጽ መጥቶ ከሰበከ በሁዋላ ከቅዱስ ይሁዳ ጋር ወደ ዛሬዋ ኢራን ሄደው ሰብከው በዚያው ሰማዕትነትን ተቀብለዋል የሚል ታሪክ አለ።

# 10-ቅዱስ ይሁዳ (ታዴዎስ)

- የታናሹ ያዕቆብ ወንድም ነው፡፡
- ጌታን «ጌታ ሆይ ለዓለም ሳይሆን ራስህን ለኛ ልትገልጥ ያለህ እንዴት ነው» ብሎ ጠየቁዋል፡፡ (ዮሐ. 14፡22)
- ስለዚህም ሐዋርያ ብዙም የሚታወቅ ነገር የለም፡፡
- አንድ መልእክት ጽፎአል፡፡

# 11-ቅዱስ ቶማስ (ዲዲሞስ)

- የገሊላ ሰው ነው:: የተዋጣለት አናጢ (ግንበኛ) ነበር::
- የስሙ ትርጉም «መንታ» ማለት ነው::
- ጌታ ወደቢታንያ አልዓዛርን ለማስነሳት ሲሔድ የአይሁድን የቀድሞ ተቃውሞ አስታውሶ «ከርሱ ጋር እንሞት ዘንድ እኛ ደግሞ እንሄድ» ሲል ተናገሮአል::
- «ጌታ ሆይ ወደምትሔድበት አናውቅም እንዴትስ መንገዱን እናውቃለን» ብሎ ስለመጠየቁ፧(ዮሐ.14:5)
- የጌታን ትንሣኤ ስለመጠራጠሩ፡ ከዚያም «ጌታዬ አምላኬም» ብሎ መመለሱ (ዮሐ. 20:25)
- ዋና ሃገረ ስብከቱ ሕንድ ነው በሰማዕትነት የሞተውም በዚያ ነው::

# የጌታን ትንሣኤ ስለመጠራጠሩ



# የእመቤታችንን እርገት ስለማየቱ



# 12-ቅዱስ ማትያስ

- ቁጥሩ ከ72 አረድዕት የነበረ ሲሆን ለሐዋርያነት በአስቆሮቱ ይሁዳ ፈንታ በዕጣ የተተካ ነው::
- ሰውነትን በጾም የመቅጣትን ትምህርት አጥብቆ ያስተምር ነበር
- በቀጰዶቅያ እና ጆረጂያ ሃይማኖትን አስፋፍቱዋል:: በዚያው ብዙ ጊዜ መከራን ከተቀበለ በሁዋላ በመስቀል ተሰቅሎ ሰማዕትነትን ተቀብሎአል::
- አጽሙ በኢየሩሳሌም ተቀምጦ በንግስት እሌኒ አማካይነት ወደ ሮም ተወስዶአል

# ዕጣ



# 13-ቅዱስ ጳውሎስ

- የመጀመሪያ ስሙ ሳውል (ሳኦል) ነው
- ከነገደ ብንያም ነው፡፡ የተወለደው ጠርሴስ ይሁን እንጂ ወላጆቹ የገሊላ ሰዎች ናቸው፡፡
- ወደ ሐዋርያነት የተጠራው ጌታ ባረገ በ8ኛው ዓመት ነው፡፡
- 14 መልእክታትን ጽፎአል፡፡
- በሰማዕትነት ያለፈው አንገቱን ተሰይፎ በ64 ዓ.ም. በሮም ከተማ ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር ነው፡፡

# የአባቶቻችን ሐዋርያት

የከበረች በረከታቸው ድል የማትነሳ
ረድኤታቸው ጥርጥር የሌለባት
ሃይማኖታቸው ከእኛ ጋር ትሁን!! አሜን